# በግብረስጋ የሚተላለፉ በሽታዎች

## (Sexually transmissible infections)

ሕክምና ማድረግ ጥሩ ሲሆን መከላከሉ የበለጠ ይሆናል

July/ሐምሌ 2003

Amharic



**ለሁላችን ማወቅ የሚያስፈልገን።**

የግብረስጋ ግንኙነት የሚፈፅም ማንኛውም ሰው ስለ በግብረስጋ የሚተላለፉ በሽታዎች (STIs) እና እንዴት ለመከላከል እንደሚቻል ማወቅ አስፈላጊ ይሆናል። በግብረስጋ የሚተላለፉ በሽታ በእኛ ላይም ሆነ ግንኙነት በምንፈፅምበት ሰው ላይ ከፍተኛ ነው።

ስለዚህም ብዙ ሰዎች የፍርሐት፤ የብስጭትና የሐፍረት ስሜት ሊያድርባቸው ይችላል። ሰዎች የሐፍረት ስሜት ካደረባቸው እርዳታ ላያገኙ ይችላሉ። ዝም ብሎ መቆየትና መጨነቅ መጥፎ ሃሳብ ሲሆን ምንም እንኳን የበሽታው ምልክት ቢጠፋም በሽታው ግን ከርስዎ ጋር እንደሚኖር ነው።

ሐኪሞች ስለ የግብረስጋ ተላላፊ በሽታዎች (STIs) የሚቀርቡትን መረጃ ሁልጊዜ በሚስጢር ይይዛሉ። ልዩ ክሊኒኮች በጣም ጥሩና በነፃ እንክብካቤ ያቀርባሉ። የክሊኒኮች ዝርዝር የሚለውን መመልከት ይሆናል።

**በግብረስጋ የሚተላለፍ በሽታ ማለት ምንድ'ነው?**

STI ወይም STD (በግብረስጋ የሚተላለፍ በሽታ) ሕመም ወይም በሽታ ሲሆን በሽታው ካለው ሰው ጋር ያለምንም መከላከያ የግብረስጋ ግንኙነት ሲደረግ ሊተላለፍ የሚችል ይሆናል። ያለምንም መከላከያ የግብረስጋ ግንኙነት ማለት ከሰውነት የሚወጣወን ቅልቅል ፈሳሽ [ደም፤ ዘር ተሸካሚ ፈሳሽ ወይም የሴት ብልት ፈሳሽ] ወደ ሌላኛው ሰው እንዳይተላለፍ የሚከላከል [ለምሳሌ ኮንዶም ወይም መገደቢያ/dam] ሳይጠቀሙ ሲከቱ ይሆናል። እነዚህ ፈሳሾች ሊተላለፉ የሚችሉት ቁላ ወይም በጋሬ የሚጠቀሙበት ኮንዶም የሌለው ወሲባዊ ግንኙነት መፈፀሚያ አሻንጉሊት በሴት ብልት፤ በፊንጣጣ ወይም በአፍ ውስጥ ሲገቡ ይሆናል።

አብዛኛው የወሲባዊ ተላላፊ በሽታዎች (STIs) የሚመጡት በጥቃቅን ሕዋሳት ማለት እንደ ቫይረስ፤ ባክቴሪያ ወይም ጥገኛ በሆኑ ነብሳት ይሆናል። አንዳንዶቹ እንደ የአባለዘር ቁማልና ኪንታሮት በቆዳ ላይ ሲገኙ አንድ ሰው የቆዳ ንከከ በሚፈጥርበት ጊዜ ሊተላለፍ ይችላል።

የወሲባዊ ተላላፊ በሽታዎች (STIs) የተለያዩ ችግሮችን ሊፈጥር የሚችል ሲሆን ከመጠነኛ ማሳከከ እስከ ለብዙ ጊዜ የሚቆይ ኃይለኛ ሕመም ሊያስከትል ይችላል። ሕክምና ካልተደረገ አንዳንዶቹ እስከ መካንነት የመሆን ችግርን ይፈጥራሉ።

አብዛኛው በወሲብ ተላላፊ በሽታዎች (STIs) ምልክት ስላላቸው በቀጥታ የሃኪም ምክር ማግኘት ይኖርብዎታል። ይሁን እንጂ አንዳንዶቹ ግልጽ የሆነ የሕመም ምልክት ስለማያሳዩ እርስዎ ለወሲባዊ ተላላፊ በሽታ ከተጠራጠሩ ምርመራ ማካሄዱ ጠቃሚ ይሆናል።

ማወቅ የሚገባዎ፡

- ብዙዎቹ በሽታዎች (STIs) ሊድኑ ይችላሉ
- ሊድኑ የማይችሉ ተላላፊ በሽታዎች (STIs) ባሁኑ ጊዜ መቆጣጠር እንደሚቻል ነው።

**የወሲባዊ በሽታ (STI) የተላለፈብዎ ከማን ነው?**

የግብረሰጋ ግንኙነት ከሚፈፅሙት ሰው ጋር በሽታው እንዳለበት ለማወቅ አይችሉም። ሰዎችን በማየት ጤናማ ይመስላሉ ነገር ግን በሽታው ሊኖርባቸው ይችላል። ማንኛውም ሰው በግብረስጋ የሚተላለፍ በሽታ እንዳለበት ለማወቅ አይችልም።

ለወሲብ ተላላፊ በሽታ(STI) ካለው ሰው ጋር መከላከያ ሳያደርጉ የግብረስጋ ግንኙነት ከፈጸሙ በበሽታው የመያዝ እድልዎ ከፍተኛ ይሆናል።

**በሽታውን መከላከል እችላለሁ ወይ?**

አዎ- 'በጥንቃቄ ወሲባዊ ግንኙነት" በመፈጸም። ግንኙነት የሚፈጽሙት ሰው ተላላፊ በሽታ ላለመኖሩ እርግጠኛ ካልሆኑ መሰረታዊ የሆነ ደንብ በመከተል የግብረስጋ ግንኙነት ከሚያደርጉት ሰው ደም፤ ስፐርም/ዘር ተሸካሚ ፈሳሽ ወይም ከሴት ብልት ፈሳሽ ወደ ሰውነትዎ እንዳይገባ መከላከል ይሆናል። ለምሳሌ ጤነኛ የሆነ ወሲባዊ ግንኙነት እንደ መሳሳም፤ በጋራ ብልትን መነካካትና ወሲብን ለማነሳሳት መተሻሸት ናቸው።

እርስዎንና ሌሎችን ለመከላከል፡

- ከወዳጅዎ ጋር ኮንዶምና ውሃ ያለው ማለስለሻ በትክክል መጠቀም
- ከወሲባዊ ፈሳሽ ጋር ምንም ግንኙነት ሳይኖር በጥንቃቄ የግብረስጋ ግንኙነት መፈጸም
- የግብረስጋ ግንኙነት አለመፈጸም

Department of Human Services

Victoria
The Place To Be

ከመደበኛ ሚስት/ባል ጋር ያለመከላከያ ወሲባዊ ግንኙነት መፍጠር ደህና ሊሆን ይችላል፡

- ሁለታችሁም ሙሉ ምርመራ በማካሄድ ከተላላፊ በሽታ ነፃ ለመሆኑ ከተረጋገጠና አንዳችሁም ከሌላ ሰው ጋር ወሲባዊ ግንኙነት የማትፈጽሙ ከሆነ እና
- እርግዝናን ለመከላከል ከፈለጋችሁ ሌላ ዓይነት የወሊድ መቆጣጠሪያ መጠቀም።

እርግጠኛ ካልሆኑ ከባለቤትዎ ጋር መነጋገርና ‘ለማያስፈራ ወሲባዊ ግንኙነት’ ለማድረግ ማሳሰብ።
ከሌላ ሰው ጋር ወሲባዊ ግንኙነት ለመፈጸም ሁለታችሁ ከተስማማችሁ ‘በጥንቃቄ የግብረስጋ ግንኙነት መፈጸም’ እንደሚኖርባችሁ ነው።

**ኮንዶሞቸን በአግባቡ እየተጠቀምኩ ነው’ወይ?**

እርስዎ ማረጋገጥ ያለብዎ፡

- ኮንዶሞችን በቀዝቃዛና ደረቅ ቦታ ፀሐይ ብርሃን በማይደርስበት ቦታ ማስቀመጥ
- የመበላሻ ቀኑ ከመድረሱ በፊት ብቻ ኮንዶሞችን መጠቀም።
- ባኮውን በጥንቃቄ በመክፈት ጥሩ ብርሃን ባለበት ካደረጉ ኮንዶሙ ላይቀደድ ይችላል። የኮንዶሙን ጫፍ በመያዝ በቆመ የወንድ ብልት/ቁላ ዙሪያ ላይ በጥንቃቄ መሸፈን ይሆናል።
- በተለይ ለፌንጢጣ ወሲብ ብዛት ያለው የውሃ ማለስለሻ መጠቀም። ያለ ማለስለሻ ግብረስጋ ግንኙነት መፈጸም ኮንዶሙን ሊቀደድ ይችላል። ኮንዶሙን ሊያዳክም ስለሚችል ከዘይት የተሰራ እንደ ሙልጭልጭ የሚል ፔትሮሊየም ወይም የህፃን ዘይት/ቤቢ ኦይል ማለስለሻ አለመጠቀም ነው።
- የወንድ ብልት ሳይተኛ/ሳይበርድ ከሴቷ ብልት ማውጣትን አለመዘንጋት ስለዚህ ኮንዶሙ ሊወልቅ አይችልም። እንዳይንጠባጠብ ኮንዶሙን ሲያወጡ ከስር መያዝ ይቻላል።
- ኮንዶሙን በድጋሜ አለመጠቀም። ከተጠቀሙ በኋላ በቆሻሻ ማጠራቀሚያ መጣል።
- በአውስትራሊያ ለሽያጭ የቀረበ ኮንዶም ብቻ መጠቀም። በቀላሉ ሊቀደድ የሚችል አነስተኛ ጥራት ያለው ኮንዶም አለመጠቀም።

**የተላላፊ በሽታ (STI) እንዳለብኝ እንዴት መናገር እችላለሁ?**

የግብረስጋ ተላላፊ በሽታ (STI) እንዳለብዎ ምንም ምልክት ላይኖር ስለሚችል ታዲያ ሁልጊዜ መጠንቀቅ አለብዎ።
ሊከሰቱ የሚችሉ ምልክቶች፡

- ከወንድ ወይም ሴት ብልት ያልተለመደ ፈሳሽ መውጣት
- በሚሸናበት ወይም የወሲብ ግንኙነት በሚፈጸምበት ወቅት ሕመም ወይም የማቃጠል ስሜት።
- ለመሽናት መቸገር
- ማቃጠል፤ ውሃ መቋጠር፤ ቁስል፤ ኪንታሮት፤ እብጠት ወይም በብልት ወይም ፊንጢጣ አካባቢ ሽፍ ያለ ነገር
- ማሳከክ ወይም በብልት ወይም ፊንጢጣ አካባቢ ጤንነት አለመሰማት
- ከወሲብ ግንኙነት በኋላ በሴት ብልት ደም መፍሰስ

**በሽታው ካለብኝ ምን ማድረግ እችላለሁ?**

በቀጥታ ሐኪምዎ ጋር መሄድ። በራሱ ይጠፋል በማለት ጊዜ መውሰድ ለሚደረገው ሕክምና ወይም ዋስትና እንዲጓተተ ያደርጋል። ምንም እንኳን ምልክቱ ቢጠፋ በሽታው ጠፍቷል ማለት አይደለም። በግብረስጋ የሚተላለፍ በሽታ (STI) ካለብዎ ወደ ሌላ ሰው እንዳያስተላልፉ በሐኪም እስከሚታዩ ድረስ የወሲብ ግንኙነት ማቆም ይገባል። የግብረስጋ ግንኙነት ካደረጉም ኮንዶም መጠቀም ይኖርብዎታል።

**እራስን መጠበቅ**

በአልኮሆል ወይም በአደገኛ እጽ ግፊት ኮንዶም አለመጠቀምና እራስን ለመጠበቅና ወደ ችግር የሚመሩትን ነገሮች ለመከላከል መዘንጋት አደጋ ላይ ሊጥልዎ ይችላል።

እራስን መንከባከብ ማለት መቻና እንዴት ኮንዶም መጠቀም እንዳለብዎት ማወቅና በጥንቃቄ ራስዎን መጠበቅ ይሆናል። የሚያደርጉትን መወሰን መቻል ከማየስፈራ የግብረስጋ ግንኙነት አፈጻጸም መገደብ አንዱ አካል ይሆናል።

**በጣም ከተለመዱት በግብረስጋ ተላላፊ በሽታዎች (STIs) የትኞቹ ናቸው?**

- ክላምዲያ/Chlamydia
- የብልት ቆዳ በሽታ/Genital Herpes
- የብልት ኪንታሮት/Genital Warts
- ጨብጥ በሽታ/Gonorrhoea
- የወፍ በሽታ/Hepatitis B
- ኤችአይቪ ወይም አመንምኔ/HIV and AIDS
- በብልት አካባቢ ቅማል/Pubic Lice (or Crabs)
- ቂጥኝ /Syphilis
- የብልት በሽታ/Trichomonas

**ከዚህ ጋር የተያያዙ በሽታዎች፡**

እነዚህ ሕክምና የሚያስፈልጋቸው የብልት በሽታዎችን ያካተተ ይሆናል። ቀጥሎ ያሉት በግብረስጋ የሚተላለፉ በሽታዎች (STIs) ላይሆኑ ይችላሉ ነገር ግን ችግሩ ሊፈጠር የሚችለው በወሲባዊ ግንኙነት ሊሆን ይችላል።

- የሴት ብልት በባክቴሪያ መለከፍ/Bacterial Vaginosis
- የወፍ በሽታ/Hepatitis C
- የሽንት ቧንቧ በሽታ/NSU
- ሽፍ ያለ ነገር/ትራሽ /Thrush

እርዳታ ካስፈለገ/ በበለጠ መረጃ ለማግኘት

በየጊዜው የሚያይዎት ሐኪም ካወቁ በግልጽ መናገር። STIs በሽታዎች የተለመዱ ስለሆነ አብዛኛው ሂኪሞች ብዙ ልምድ ይኖራቸዋል። እንደማንኛውም ጊዜ የሕክምና ክፍያ ይኖረዋል።

መደበኛ ሂኪምዎን ለማናገር ደስተኛ ካልሆኑ በነፃ ለስልክ መረጃ አቅርቦት መደወል።

**የሜልበርን ግብረስጋ ግንኙነት ማእከል**
The Melbourne Sexual Centre
580 Swanston St. Carlton
ስልክ: 9347 0244 [ለደንቆሮዎች/TTY ያጠቃለለ ይሆናል]
ከከተማ ውጭ የነፃ ስልክ 1800 032 017

የሚቀርበው አገልግሎት በነፃና በሚስጢር የተጠበቀ ይሆናል።
ሰራተኞች በስልክ ወቅታዊ የሆኑ ምክሮችን ሲያቀርቡ እርስዎን ለማየት ቀጠሮ ማቀናጀት ወይም ባካባቢዎ ባለ ሄኪም እንዲሄዱ ምክር ይለግስዎታል።

በሚቀጥለው ገጽ ላይ ዝርዝር አገልግሎቶች ቀርበዋል።

**በሞላው ስተዳደር ግዛት አገልግሎት ለማግኘት፡**

**AIDSLINE**
በስልክ ስለ ኤችአይቪ/አመንምኔ፣ ተላላፊ በሽታና ወሲባዊ ጤና በተመለከተ ምክር ለማግኘት፡
በስልክ፡ 9347 6099
ከከተማ ውጭ የነፃ ስልክ 1800 133 392
TTY 1800 032 665

**Hepatitis C Helpline**
**ለወፍ በሽታ እርዳታ ማቀረቢያ መስመር**
በስልክ ምክር ለማግኘት፣ መረጃና ወደሚመለከተው ለማስተላለፍ፡
በስልክ፡ 9349 1111
ከከተማ ውጭ የነፃ ስልክ 1800 800 241
ለቬትናም ቋንቋ ተናጋሪ 1800 456 007
TTY 1800 032 665

**Victoria Aids Council/Gay Men's Health centre**
**በቪክቶሪያ የአመንምኔ ምክር ሰጪ/የወንዳገረድ ጤና ማእከል**
6 Claremont St, South Yarra 3141
በስልክ፡ 9865 6700
የነፃ ስልክ 1800 134 840
TTY 9827 3733
www.vicaids.asn.au

**Access Information Centre at The Alfred**
**በአልፍረድ መረጃ ማቀረቢያ ማእከል**
Commercial Rd
Prahran 3181
በስልክ፡ 9276 6993
Email:
access@alfred.org.au
www.accessinfo.org.au

**The Centre Clinics C/-Northcote Community Health Centre**
**የክሊኒክ ማእከል/ኖርዝኮት ማሕበረሰብ ጤና ማእከል**
42 Separation St
Northcote 3070
በስልክ፡ 9481 7155

**St Kilda**
46 Acland St,
St Kilda 3182
በስልክ፡ 9525 5866

**Family Planning Victoria**
**በቪክቶሪያ የቤተሰብ ምጣኔ**
901 Whitehorse Road
Box Hill 3128
ክሊኒክና ትምህርት
በስልክ፡ 9257 0100
Email: fpv@fpv.org.au

**Action Centre (Youth)**
**ለወጣቶች እንቅስቃሴ ማእከል**
Level 1, 94 Elizabeth St
Melbourne 3000
ክሊኒክና ትምህርት
በስልክ፡ 9654 5766 ወይም 1800 013 952

**Hepatitis C Council of Victoria**
**በቪክቶሪያ የወፍ በሽታ መማክርት**
Suite 5, 200 Sydney Road
Brunswick 3056
በስልክ፡ 9380 4644
ከከተማ ውጭ ሆኖ በነፃ ለመደወል 1800 703 003

**Rural STI Clinics: The Annexe Sexual Health Family Clinic Ballarat Community Health**
**በገጠር በግብረስጋ ተላላፊ በሽታ ክሊኒኮች፡ የቤተሰብ ክሊኒክ ለባላራት ማሕበረሰብ ጤና**
710 Stut Street
Ballarat 3350
በስልክ፡ 5333 1635

**STI Clinics: Bendigo Community Health Service**
**በግብረስጋ ተላላፊ በሽታ ክሊኒኮች፡ የባላራት ማሕበረሰብ ጤና አገልግሎት**
3 Seymouret Street
Eaglehawk 3556
በስልክ፡ 5434 4300

**STI Clinic: Barwon Health**
**በግብረስጋ ተላላፊ በሽታ ክሊኒክ፡ የባርዎን ጤና አገልግሎት**
Geelong Hospital
Swanston Street
Geelong 3220
በስልክ፡ 5221 4735

**STI Clinic Vermont St Health Clinic**
**በግብረስጋ ተላላፊ በሽታ ክሊኒክ፡ የቨርሞንት መንገድ ጤና ክሊኒክ**
4 Benson Court Street
Wodonga 3690
በስልክ፡ 6056 1589

**STI Clinic: Latrobe Regional Hospital (Outpatient Dept)**
**በግብረስጋ ተላላፊ በሽታ ክሊኒክ፡ የላትሮብ ግዛት ሆስፒታል [የተመላላሽ በሽተኛ ክፍል]**
Cnr Princess Highway & Village Way
Traralgon 3844
በስልክ፡ 5173 8000